የታጠቅን ፡ መሆን ፡ እንዳለብን ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ነግረውናል ። እንግዲህ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ትልቅ ፡ እንድትሆን ፡ ወጣቶቿ ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ጠንካራ ፡ መንፈስ ፡ እየተመሩ ፡ ተምረው ፡ ለመሥዋዕትነት ፡ የታጠቁ ፡ መሆን ፡ እንደሚገባቸው ፡ ያልተረዱ ፡ አይገኙም ።

በዚህ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ ዛሬ ፡ እዚህ ፡ ከቆምነው ፡ አብዛኞቻችን ፡ በግርማዊነትዎ ፡ ሰፊ ፡ ችሮታ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እዚህ ፡ ደረጃ ፡ የደረስን ፡ እረኞች፡ ሆነን የምንቀር ነበርን ። ይህንንም ፡ ጭምር ፡ እያስታወስን ፡ አገራችንን ፡ ለማገልገልና ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ለመርዳት ፡ የታጠቅን ፡ መሆን ፡ እንደሚገባን ፡ ተረድተናል ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ዛሬ ፡ ከዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ የቀረብን ፡ ለጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከምንወዳት ፡ አገራችንንና ፡ አባት ፡ ሆነው ፡ ካሳደጉን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ከመለየታችን ፡ በፊት ፡ መንፈሳችንን ፡ የሚያጠነክረውን ፡ የግርማዊነትዎን ፡ ዓይን ፡ ለማየትና ፡ ድምፅ ፡ ለመስማት ፡ ነው ።

* * *

ለ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

እንደምታውቁት ፡ ይህ ፡ ያለንበት ፡ ዓለም ፡ የተውሶ ፡ ቤት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለዘለዓለም ፡ የምንኖርበት ፡ ቤት ፡ አይደለም ። በዚህ ፡ የተውሶ ፡ በሆነው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በምቾትም ፡ ያለምቾትም ፡ ሊኖርበት ፡ ይቻላል ።

ሰው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለመኖር ፡ የሚችለው ፡ እግዚአብሔር ፡ እስከወሰነለት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በራሱ ፡ እስከፈለገበት ፡ ጊዜ ፡ ድረስ ፡ እንዳልሆነ ፡ የታወቀ ፡ ነው ።

ሰው ፡ በተፈጥሮ ፡ ታላቅ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ታላቅነቱ ፡ ላይ ፡ ግን ፡ ትምህርትን ፡ ካልጨመረ ፡ ራሱን ፡ ከማሳነሱ ፡ በላይ ፡ ዘሩን ፡ ጭምር ፡ በማሳነስ ፡ ጐስቋላ ፡ ያደርጋል ።

ይህም ፡ አዲስ ፡ ያይደለ ፡ በኛው ፡ ዘመን ፡ የሆነና ፡ የታየ ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ሰው ፡ በሚኖርበት ፡ በዚህ ፡ የተውሶ ፡ በሆነ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚቆይበት ፡ ጊዜ ፡ ለተወሰነ ፡ ዘመን ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ አይገባውም ።

የሰው ፡ ልጅ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በሚኖር



በት ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ከሚያስፈልጉት ፡ ነገሮች ፡ አንዱ ፡ ትምህርት ፡ ሆኖ ፡ ይገኛል ።

ትምህርት ፡ ለሰው ፡ ልጅ ፡ የሚሰጠውን ፡ ታላቅ ፡ ጥቅም ፡ ያህል ፡ ያለመማርም ፡ የሚያደርስበትን ፡ ጉዳት ፡ የዚህኑ ፡ ያህል ፡ እንደሆነ ፡ ግልጥ ነው ።

ለመማር ፡ መማር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ የሚጠቅም ፡ እንደሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አዳጋች ፡ ነገር ፡ አይደለም ። መማር ፡ ማወቅን ፡ ሲያስገኝ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ በበኩሉ ፡ ራስን ፡ ከጉዳት ፡ ጠብቆ ፡ አላዋቂ ፡ ከመሆን ፡ ከማዳኑም ፡ በላይ ፡ ለወገን ፡ እንደራስ ፡ ማሰብን ፡ በማትረፍ ፡ መመቅኘት ፡ ያርቃል ።

እናንተ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጆች ፡ ትሆናላችሁ ፡ ምናልባትም ፡ አልተወለዳችሁ ፡ ይሆናል ። የትምህርት ፡ ቤት ፡ ያቋቋምነው ፡ ከሐያ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ገና ፡ በአልጋ ፡ ወራሽነታችን ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

በዚያን ፡ ዘመን ፡ ትምህርት ፡ ማቋቋም ፡ በጀመርንበት ፡ ጊዜ ፡ ገጥሞን ፡ የነበረ ፡ መሰናክል ፡ ተስፋ ፡ የሚያስቆርጥና ፡ ይህንን ፡ ያህላል ፡ የማይሉት ፡ ግምት ፡ የሌለው ፡ ነበር ።

ይሁን ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ መሰናክሉ ፡ ከፍ ፡ ያለና ፡ አስቸጋሪ ፡ ሆኖ ፡ ቢታይም ፡ ተስፋ ፡ ባለመቁረጥ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ በቆራጥነት ፡ በመታገላችን ፡ እናንተንና ፡ ከናንተም ፡ በፊት ፡ ተምረው ፡ ለወግ ፡ ለማዕርግ ፡ የደረሱትን ፡ ብዙ ፡ ልጆች ፡ በትምህርት ፡ መውለዳችንን ፡ ስናስታውስ ፡ ደስ ፡ ይለናል ። ይህ ፡ የተጀመረው ፡ የትምህርት ፡ ፕሮግራም ለአሁኑ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከኛም ፡ በኋላ ፡ ቢሆን ፡ በዚሁ ፡ መንገድ ፡ መቀጠል ፡ ያለበት ፡ ነገር ፡ ነው ።

እናንተም ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄዳችሁ ፡ የምትማሩት ፡ ትምህርት ፡ ለግል ፡ ኑሮ ፡ ማዳበሪያ ፡ ሳይሆን ፡ ለጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ የሚካፈልና ፡ የሚጠቅም ፡ መሆን ፡ እንዳለበት ፡ ማወቅ ፡ አለባችሁ ።

አሁን ፡ እናንተ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ሄዳችሁ ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት፡ እንድትማሩ ፡ የምንልካችሁ ፡ በየተመረጣችሁበት ፡ ትምህርት ፡ በትጋት ፡ ተምራችሁ ፡ ለሀገራችሁ ፡ ታማኝ ፡ ዘበኛ ፡ ለመሆን ፡ እንድትበቁ ፡ በሙሉ፡ ልብ ፡ ተስፋ ፡ በማድረግና ፡ በመመኘት ፡ ነው ።

አንድ ፡ ታማኝ ፡ ዘበኛ ፡ ጠላትን ፡ ከበሩ ፡ አያስደርስም ፡ ወሰኑን ፡

አያስደፍርም ፡ ለሀገሩና ለወገኑ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታማኝ ፡ በመሆን ፡ የተጣለበትን ፡ አደራ ፡ ለባለ ፡ ተራው ፡ አስተላለፈ ፡ ድረስ ፡ ተግቶና ፡ ነቅቶ ፡ ሀገሩን ፡ በመጠበቅ ፡ ወገኑን ፡ ያስከብራል ፡ መሪውን ፡ ያኰራል ።

የትምህርት ፡ መሣሪያነቱ ፡ ዕውቀትን ፡ መገብየት ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ሀገርንና ፡ ወገንን ፡ ለመውደድ ፡ ዋና ፡ ጠቃሚ ፡ መሣሪያ ፡ መሆኑን ፡ መዘንጋት ፡ የለባችሁም ። ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ አገርን ፡ መውደድ ፡ ታላቅ ፡ እውቀት ፡ ነውና ፡ ሀገራችሁን ፡ ከራሳችሁ ፡ አብልጣችሁ ፡ መውደድ ፡ አለባችሁ ።

አሁን ፡ በተናገራችኋቸው ፡ መልካም ፡ ቃሎች ፡ ደስ ፡ እንዳለን ፡ ለተነሳንበት ፡ ታላቅ ፡ ዓላማ ፡ በቅታችሁ ፡ በማየታችን ፡ ወደፊትም ፡ ትምህርት እንድትገበዩ ፡ ከላክናችሁ ፡ ስፍራ ፡ ተምራችሁ ፡ በደህና ፡ እንድትመለሱ ፡ የናንተን ፡ አገልግሎት ፡ የምትጠብቀው ፡ ውድ ፡ አገራችሁን ፡ ለማገልገል ፡ እንድትበቁ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳይለያችሁ ፡ አደራ ፡ እንላችኋለን ።

---

# 623

ለቴክኒክ ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚሄዱ ፡ ሐያ ፡ ሁለት ፡ ተማሪዎች ፡ ነሐሴ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፰ ፡ ሰዓት ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከወጣቶቹ አንዱ ፡ ሉል ፡ ሰገድ ፡ ዓለማየሁ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

ሀ) የወጣቱ ፡ ተማሪ ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ከዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቆሜ ፡ በራሴና ፡ አብረው ፡ ለትምህርት ፡ በሚጓዙ ፡ ጓደኞቼ ፡ ስም ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ስናገር ፡ ታላቅ ፡ ዕድሌ ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የማንኛውም ፡ ክፍለ ፡ ዓለም ፡ ሥልጣኔ ፡ መሠረቱ ፡ የወደቀው ፡ በትምህርት ፡ ላይ ፡ ነው ። ግርማዊነትዎም ፡ ይህንኑ ፡ በመገንዘብ ፡ ሌሎች ፡ የምዕራብ ፡ አገሮች ፡ እደረሱበት ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ አገራችን ፡ እንድት



ደርስ ፡ ከቀድሞ ፡ ጀምረው ፡ ይደክማሉ ። ሌት ፡ ከቀንም ፡ ያለዕረፍት ፡ ተግተው ፡ መሥራትዎ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ይኸው ፡ አሁን ፡ ካለችበት ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ አድርሷት ፡ ይታያል ። ወጣቶችዋም ፡ በሙሉ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥትዎ ፡ የትም ፡ አገር ፡ የማይደረገውን ፡ የነፃ ፡ ትምህርት ፡ እያገኙ ፡ በአሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ የሚበዛውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በአዛዥነትም ፡ በታዛዥነትም ፡ ይዘውት ፡ ይገኛሉ ። ለዚሁም ፡ ሁሉ ፡ በምርቱ ፡ የተደሰትን ፡ ገበሬ ፡ የምሥራች ፡ የማለት ፡ የበለጠ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በተማሪዎች ፡ ብዙ ፡ ምርት ፡ የተደሰቱትን ፡ የምሥራች ፡ ማለት ፡ ይገባናል ።

ግርማዊነትዎ ፡ በትጋት ፡ ኢትዮጵያ ፡ በአሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ካለው ፡ የትምህርትና ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ አድርሰዋታል ። በትምህርት ፡ ታሪክ ፡ ውስጥ ፡ በማንኛውም ፡ ምዕራፍ ፡ ብንመለከት ፡ ያለትግልና ፡ ያለመከራ ፡ ማንኛውም ፡ አሁን ፡ በሥልጣኔ ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አገር ፡ የሥልጣኔም ፡ አባት ፡ ነኝ ፡ እንደ ፡ ኢትዮጵያችን ፡ በጥቂት ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የትምህርትና ፡ የሥልጣኔ ፡ ደረጃ ፡ የተቀዳጀ ፡ የለም ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

እኛም ፡ ወጣቶች ፡ ልጆችዎ ፡ ትምህርታችንን ፡ በሰፊው ፡ ገፍተን ፡ ወደፊት ፡ አገራችንን ፡ እንድንረዳ ፡ ይህን ፡ ዕድል ፡ ያገኘነው ፡ አስቀድመን ፡ ከዓመት ፡ በሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በወዳጅነት ፡ ካፈራቸው ፡ ካሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ በተላኩ ፡ ቴክንሺያን ፡ ጋር ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ስናጠና ፡ ከቆየን ፡ በኋላ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ባዘጋጁልን ፡ ድርጅት ፡ መሠረት ፡ ለመማር ፡ መሄዳችን ፡ ስለሆነ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ልማትና ፡ ዕድገት ፡ ያለ ፡ እንቅልፍ ፡ ለሚሠራው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ በሰው ፡ አፍ ፡ ሊነገር ፡ የማይቻል ፡ ምስጋና ፡ እናቀርባለን ።

በዚህም ፡ ዓይነት ፡ አያያዝ ፡ ኢትዮጵያችን ፡ ጥቂት ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ከታወቁትና ፡ ልቀው ፡ ከሚታዩት ፡ የዓለም ፡ መንግሥታት ፡ አንዷ እንደምትሆን ፡ የሁላችን ፡ ተስፋ ፡ ነው ።

ዕድሜ ፡ ለግርማዊ ፡
ዕድሜ ፡ ለግርማዊት ፡

ዕድሜ ፡ ለልዑላን ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፡
ኢትዮጵያ ፡ በነፃነቷ ፡ ለዘለዓለም ፡ ትኑር ።

❋ ❋ ❋

ለ) ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ።

መጀመሪያ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ማቋቋም ፡ ስንጀምር ፡ እናንተ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ልጆች ፡ ትሆናላችሁ ፡ ወይም ፡ አልተወለዳችሁም ፡ ይሆናል ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እንደአሁኑ ፡ ከፍተኞች ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሳይኖሩ ፡ ሥራውን ፡ መጀመሩ ፡ ስለነበረ ፡ የኤሌሜንታሪን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ብቻ ፡ በማቋቋማችን ፡ ብዙ ፡ ችግር ፡ እየገጠመን ፡ ተስፋ ፡ ሳንቆርጥ ፡ የገጠመንን ፡ ችግር ፡ ሁሉ ፡ አሸንፈን ፡ ከፍጻሜ ፡ ልናደርሰው ፡ ቻልን ። ይኸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ነው ። የሚሠራው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመልካም ፡ ስለሆነ ፡ የሚወጠነው ፡ ይኸው ፡ ዛሬ ፡ ለኤሌሜንታሪ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ለሴከንደሪና ፡ ለኮሌጅ ፡ ለዩኒቨርሲቲም ፡ የበቁ ፡ ተማሪዎች ፡ ለማፍራት ፡ ከቻልንበት ፡ ጊዜ ፡ ላይ ፡ ደርሰናል ። በተማሩት ፡ ልጆች ፡ ለአገራችን ፡ ስለተጠቀምንባቸው ፡ በዚህም ፡ ደስ ፡ ብሎናል ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ ከአሁኑ ፡ ይልቅ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ለኤሌሜንታሪ ፡ ብቻ ፡ የሚሆን ፡ ልጆች ፡ ለማስተማር ፡ የትምህርትን ፡ ሥራ ፡ ስናቋቁም ፡ የፈጸምነው ፡ ሥራ ፡ አሁን ፡ ስናስታውሰው ፡ የበለጠ ፡ ደስታ ፡ ይሰጠናል ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የኤሌሜንታሪ ፡ ትምህርት ፡ ስንከፍት ፡ በጦር ፡ በኩልም ፡ መርጠን ፡ ያስተማርናቸው ፡ ልጆች ፡ የክብር ፡ ዘበኛም ፡ ብለን ፡ ስንቆረቁር ፡ በጦር ፡ ሠራዊትም ፡ ውስጥ ፡ ሆነው ፡ ያገልግሎታቸውን ፡ ፍሬ ፡ አሳይተዋል ። አሁንም ፡ በጦር ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ የጦር ፡ አካዳሚና ፡ ያየር ፡ የባሕር ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ እንዲማሩ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ልጆች ፡ ከብዙ ፡ ዘርፍ ፡ በመምረጥ ፡ ላይ ፡ ነን ።

ተማሪ ፡ ቤት ፡ እንደ ፡ ትልቅ ፡ ዛፍ ፡ ነው ። ዛፍ ፡ በላዩ ፡ ብዙ ፡ ቅርንጫፎች ፡ እንዳሉት ፡ ሁሉ ፡ ትምህርትም ፡ እንደዚሁ ፡ በየበኩላቸው ፡ ስፔሲያሊቴ ፡ የሚጠይቁ ፡ እንደሕክምና ፡ መሐንዲስነት ፡ የመርከብ ፡ የጦር ፡ የፖሊስ ፡ የአየር ፡ የባሕር ፡ ሌሎችም ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉ ፡ ተግባሮች ፡ ስለሚገኙበት ፡ ሁሉም ፡ ሲደመሩ ፡ ለአገር ፡ ጠቃሚነት ፡ አላቸው ፡ እናንተም ፡ በያንዳንዱ ፡ ትምህርት ፡ ሴቶች ፡ ሳይቀሩ ፡ ይኸው ፡ በሰፊው ፡

Sig. 10 F



አቅድ ፡ ተይዟል ። እንደናንተ ፡ ተማሪዎች ፡ በሚሊቴርና ፡ በሲቢል ፡ ወደ ፡ አሜሪካና ፡ ወደሌላም ፡ ዓለም ፡ ክፍል ፡ ልከናል ። የትምህርት ፡ ጥቅሙ ፡ ሁለት ፡ ዓይነት ፡ ነው ። አንደኛው ፡ ይኸው ፡ እናንተም ፡ እንደጠቀሳችሁት ፡ አገራችንን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በዓለም ፡ ፊት ፡ በሌሎችም ፡ አገሮች ፡ አንፃር ፡ ከፍ ፡ ብላ ፡ እንድትታይ ፡ ያደርጋል ። ሁለተኛ ፡ ትምህርት ፡ ከሰው ፡ ጠባይ ፡ ጋር ፡ ተዋህዶ ፡ የሚኖር ፡ እንደመሆኑ ፡ መጠን ፡ ደግሞ ፡ ለክፉም ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ።

ይህም ፡ ማለት ፡ ወደ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ የሚመራ ፡ አንዳንድ ፡ ሲገኝ ፡ ክፋትን ፡ ብቻ ፡ የሚሠራና ፡ ክፋትን ፡ ብቻ ፡ የሚያስብ ፡ ሆኖ ፡ እንዲያውም ፡ ክፉ ፡ በሽታ ፡ ወደሚወልዱት ፡ የአገር ፡ ልጆች ፡ ከደም ፡ ጋር ፡ ተያይዞ ፡ እንደሚተላለፍ ፡ ሁሉ ፡ ክፉም ፡ ሰው ፡ የክፋት ፡ ጠባይን ፡ በራሱ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ከሱ ፡ ወደሚወለዱት ፡ ወገኖቹ ፡ ልጆች ፡ እየተላለፈ ፡ መንፈሳቸውን ፡ ይመርዘዋል ። በደግነት ፡ መንገድ ፡ ሲሄድ ፡ ደግሞ ፡ ያንኑ ፡ ያህል ፡ መልካም ፡ ፍሬ ፡ ይሰጣል ። ስለዚህ ፡ ትምህርት ፡ እስከ ፡ ዕድሜ ፡ መጨረሻ ፡ ከሰው ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ ተቆራኝቶ ፡ የሚኖር ፡ ወረት ፡ የማይደረግበት ፡ ነው ።

እኛም ፡ ከአሁን ፡ በፊት እንደተናገርነው ፡ ሁሉ ፡ የትምህርት ፡ ቤታችንና ፡ የተማሪዎቻችን ፡ ደረጃ ፡ ከፍ ፡ ለማድረግ ፡ የምንፈጽመውን ፡ ጥረት ፡ እንቀጥልበታለን ፡ እንጂ ፡ እስከ ፡ ሕይወታችን ፡ መጨረሻ ፡ አናቋርጥም ።

ለትምህርት ፡ መመረጥ ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለተመረጡበትም ፡ ጠቃሚ ፡ ሆኖ ፡ መገኘት ፡ የሚያስደስት ፡ ይሆናል ። ዕድሉና ፡ ባሕሪው ፡ እንደመረጠው ፡ እናንተም ፡ በጀመራችሁት ፡ ትምህርት ፡ ፈጽማችሁ ፡ እንደመጣችሁ ፡ በሥራ ፡ እየገፋችሁ ፡ በመሄድ ፡ ከምትመኙት ፡ ደረጃ ፡ ደርሳችሁ ፡ በሥራ ፡ እየረዳችሁን ፡ አገራችሁን ፡ ለመጥቀምና ፡ ለማገልገል ፡ እንዲያበቃችሁ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንለምንላችኋለን ።

---

# 624

ትምህርታቸውን ፡ ፈጽመው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የተመለሱ ፡ ፯ ፡ ተማሪዎች ፡ ነሐሴ ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በ፫ ፡ ሰዓት ፡ ተኩል ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ እጅ ፡ ከነሱ ፡ በኋላ ፡ ከተማሪዎቹ ፡ አንዱ ፡ አበበ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ በራሱና ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገ

ረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ።

ሀ) የተማሪው ፡ ንግግር ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ የደረሰበት ፡ መራራ ፡ ኀዘንና ፡ መላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ተካፋይ ፡ ሆኖ፡ የተገኘውና ፡ አሁንም ፡ ሆነ ፡ የሚገኘው ፡ የተወዳጁ ፡ ልጅዎና ፡ መስፍናችን ፡ የልዑል ፡ መኰንን ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ በመላው ፡ ኢትዮጵያውያንና ፡ ኢትዮጵያዊት ፡ ልቦና ፡ ጥሎ ፡ የሄደው ፡ ከባድ ፡ የኀዘን ፡ ጥንስሱ ፡ ጊዜውን ፡ እንደማለፉ ፡ መጠን ፡ እየኮመጠጠና ፡ እየመረረ ፡ ሄዷል ።

እኛም ፡ ዛሬ ፡ በዚህ ፡ በገናናው ፡ ዙፋንዎ ፡ ፊት ፡ ቀርበን ፡ ከ፴ ፡ ከ፳ና፥ ከ፲ ፡ ዓመታትም ፡ ይበልጥ ፡ ተለይቶን ፡ የነበረውን ፡ ብርሃናዊ ፡ ገጽዎን ፡ ስንመለከት ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ የተመደቡልንን ፡ ትምህርቶቻችንን ፡ የጨረስን ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ የልዑል ፡ ጌታችን ፡ ድንገተኛ ፡ ሞት ፡ ያቀራረባችንን ፡ መልክ ፡ ሲያጠቁረውና ፡ የኀዘኑ ፡ ደመና ፡ በሁላችንም ፡ እራስ ፡ ላይ ፡ ሲያንዣብብ ፡ ስለሚታይ ፡ ልባዊ ፡ ኀዘን ፡ ተካፋይነታችንን ፡ እየገለጥን ፡ ግርማዊነትዎንና ፡ ግርማዊትን ፡ ልዕልት ፡ ባለቤታቸውንም ፡ ጭምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጥናችሁ ፡ በማለት ፡ ከዚህ ፡ የሚለጥቁትን ፡ ጥቂቶች ፡ መስመሮች ፡ እንድናገር ፡ ይፈቀድልኝ ፡ ዘንድ ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ስለምን ፡ በታላቅ ፡ ትህትናና ፡ ፍርሃት ፡ ነው ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

የዛሬ ፡ ፲ ፡ ዓመት ፡ ገናናው ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ክብርንና ፡ ሞገስን ፡ ተጐናጽፎ ፡ አሜሪካንና ፡ የተወሰኑ ፡ የኤውሮፓ ፡ አገሮችን ፡ በጐበኘ ፡ ጊዜ ፡ ከጥንታዊነቷና ፡ ከታሪካዊቷ፡ ዮናናውያን ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፡ አቴን ፡ ፳ ፡ ቀናት ፡ ያህል ፡ አሳልፎ ፡ ነበር ። በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አቴን ፡ ይገኝ ፡ በነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ሌጋስዮን ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ በክቡር ፡ ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ወሰን ፡ ኃይሉ ፡ መልካም ፡ ፈቃድና ፡ በሌጋስዮኑ ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ በአቶ ፡ ሐጎስ ፡ ተወልደመድኅን ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አስተርጓሚ ፡ ለመሆን ፡ ዕድል ፡ አጋጥሞኝ ፡ ስለነበረ ፡



በኢትዮጵያ ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ የሚደክመውን ፡ ግርማዊነትዎን ፡ በኒዚያ ፡ በአምስ ፡ ቀናት ፡ ውስጥ ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ ላውቀው ፡ የማልችለውን ፡ ያህል ፡ ለማወቅ ፡ ቻልኩ ፡ ኀበ ፡ ሀሎ ፡ መዝገብከ ፡ ህየ ፡ ትሄሎ ልብከ ፡ እንደተባለው ፡ የትም ፡ የት ፡ ሆኖ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ የሚያስበው ፡ ኢትዮጵያችንን ፡ ነበር ።

ትዝ ፡ እንደሚለኝ ፡ አቶ ፡ ከበደ ፡ ሚካኤል ፡ ከፈረንሣይ ፡ አገር ፡ መጥተው ፡ ግርማዊነትዎን ፡ ለመገናኘት ፡ የሄሮድስ ፡ አንታኪዊ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ በተባለው ፡ ማረፊያ ፡ ውስጥ ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ተገኝተው ፡ ሲቀበላቸው ፡ እንደምነህ ፡ ከበደ ፡ መቼ ፡ መጣህ ፡ ባየናቸው ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ የሚሠራውን ፡ የጥበብ ፡ ሥራ ፡ እያየህ ፡ አትቀናም ፡ ወይ ፡ እኔን ፡ ለሀገሬ ፡ ዕድገትና ፡ ልማት፡ እንዲህ ፡ እንድደክም ፡ ያደረገኝ ፡ ለጥበብ ፡ ያለኝ ፡ ቅናት ፡ ነው ፡ ብለው ፡ በተናገሩት ፡ ጊዜ ፡ የኢትዮጵያዊነት ፡ ስሜት መነሻውና ፡ መድረሻው ፡ መጀመሪያውና ፡ መደምደሚያው ፡ ይህ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ ቃል ፡ ሆኖ ፡ ረሀብንና ፡ ጥምን ፡ በሰው ፡ አገርም ፡ ከችግራችንና ፡ ከ ቀለማችን ፡ ልዩነት ፡ የደረሰብኝን ፡ መከራዎች ፡ ሁሉ ፡ ታግሼ ፡ እፍጻሜ ፡ እንዲደርስ ፡ የረዳኝ ፡ ታላቅ ፡ መሰላል ፡ ሆኖኝ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ አብረውኝ ፡ በሚገኙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ወንድሞቼ ፡ የግርማዊነትዎ ፡ አርአያነት ፡ ደብዳቤያቸውና ፡ አጽናኛቸው ፡ እንደነበረ ፡ አምናለሁ ።

ግርማዊ ፡ ሆይ ።

ግርማዊነትዎ ፡ ሌት ፡ ከቀን ፡ የሚደክመውና ፡ ለሀገራችን ፡ ይህን ፡ የምናየውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሠርቶ ፡ ቅንዓት ፡ ቢሰማው ፡ እኛ ፡ ለሀገራችን ምንም ፡ ያልሠራንላት ፡ ልጆቿ ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ ስሜት ፡ ሊኖረን ፡ ያስፈልጋል ፡ ይሆን ? ይህን ፡ ወደፊት ፡ ሥራችንን ፡ ይግለጠው ፡ ስል ፡ ስሜቱ ፡ የሁላችንም ፡ መሆኑን ፡ ሳልጠራጠር ፡ ነው ። እነሆ ፡ ዛሬ ፡ ጥቂቶቻችን ፡ ግርማዊነትዎ ፡ ሲኰተኩቱንና ፡ የዕውቀት ፡ ውሀን ፡ ሲያጠጡን ፡ ኖሩ ፡ ከቡቃያነትና፡ከችግርነት ፡ አልፈን፡ፍሬ፡ሆነን፡ግርማዊነትዎ፡ፊት ፡ እንገኛለን ። ለኛም ፡ ፍሬ ፡ መሆን ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ፡ እመሬት ፡ ወድቀንና ፡ በስብሰን ፡ የፀሐዩን ፡ ቃጠሎ ፡ የሌሊቱን ፡ ቁርና ፡ የቀኑን ፡ ሐሩር ፡ ችለን ፡ ፍሬ ፡ ማፍራት ፡ አለብን ።

ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

443 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ሎንዶን ፡ በቢ.ቢ.ሲ ፡ የሬዲዮ ፡ ጣቢያ ፡ በቴሌቪዥን ፡ ታይተው ፡ ያደረጉት ፡ ንግግር ። . . . . . . . . . ፲፱፻፴፯

444 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ከኢትዮጵያ ፡ ዓርበኞች ፡ ጋር ፡ የዘመቱትን ፡ የእንግሊዝ ፡ ዓርበኞች ፡ ክለብ ፡ ከጐበኙ ፡ በኋላ ፡ በተደረገው ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ። . . . . . . . . . ፲፱፻፴፯

445 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. በፈረንሳይ ፡ አገር ፡ በኤሊዜ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት፡ በተደረገላቸው ፡ ታላቅ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱፻፴፰

446 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ስለ ፡ ክቡር ፡ የፈረንሳይ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክብር ፡ ፓሪስ ፡ ባለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ ኤምባሲያቸው ፡ ባደረጉት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ። . . ፲፱፻፵፪

447 ጥቅምት ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. የፈረንሳይ ፡ መንግሥት ፡ የውጭ ፡ ጉዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ባደረጉት ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . ፲፱፻፵፫

448 ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሐያ ፡ አራተኛ ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ሲከበር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በግርማዊነታቸው ፡ ስም ፡ ለፓርላሜት ፡ ያቀረቡት ፡ የዙፋን ፡ ቃል ። . . . . . ፲፱፻፵፭

449 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. ግርማዊት ፡ ንግሥት ፡ ጁሊያና ፡ ስለግርማዊነታቸው ፡ ክብር ፡ ባደረጉላቸው ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ንግሥት ፡ ጁሊያና ፡ ላደረጉት ፡ ንግግር ፡ ከግርማዊነታቸው የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱፻፵፯



ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

450 የጀርመን ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቴዎዶር ፡ ሔውስና ፡ ቻንስለሩ ፡ ዶክተር ፡ አደናወር ፡ ጥቅምት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. በሻምቡርግ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ባደረጉት ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . ፲፱፻፵፰

451 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. የቦን ፡ ከተማ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤትን ፡ ሲጐበኙ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱፻፶፩

452 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. በፍሬንድሪኽ ፡ ዊልሄልም ፡ ዩንቨርሲቲ ፡ የክብር ዶክተርነት ፡ ዲግሪ ፡ ሲቀበሉ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . ፲፱፻፶፪

453 የጀርመን ፡ ፌዴራል ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ቻንስለር ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. በመኖሪያ ፡ ቤታቸው ፡ ስለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ባደረጉት፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱፻፶፫

454 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኅዳር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም ስለ ፡ ጀርመን ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክብር ፡ በኤምባሲያቸው ፡ ባደረጉት ፡ ታላቅ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ያደረጉት ፡ ንግግር ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱፻፶፬

455 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኅዳር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም የዱስልዶርፍ ፡ ከተማን ፡ ሲጐበኙ ፡ የዌስትፌልያ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ስለ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ክብር ፡ ባደረጉት ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። ፲፱፻፶፭

456 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኅዳር ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም ሐምቡርግን ፡ ሲጐበኙ ፡ ስለ ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ክብር፡ በተደረገው ፡ ግብዣ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠው ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፱፻፶፯

| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 504 | ነሐሴ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ. ም. ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ስለ ፡ ፖሊስ ፡ ሠራዊት ፡ መልካም ፡ አኗኗርና ፡ ስለ ፡ ጤናው ፡ አጠባበቅ ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ። . . | ፲፩፻፪ |
| 505 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. በልዕልት ፡ ፀሐይ ሆስፒታል ፡ ተገኝተው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ለፈጸሙ ፡ ለ፲፪ ፡ ነርሶች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሲሰጡ ፡ የሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ ተጠባባቂ ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ባላምባራስ ፡ ማኅተመ ፡ ሥላሴ ፡ ወልደ ፡ መስቀልና ፡ የሆስፒታሉ ፡ ዲሬክተር ፡ ዶክተር ፡ ሆልማን ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተደረገ ፡ ንግግር ። . . . . . . . . . . | ፲፩፻፮ |
| 506 | ለከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ የሚሔዱት ፡ ፳፪ ፡ ወጣቶች ፡ መስከረም ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ፡ ከወጣቶቹ ፡ አንዱ ፡ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረውና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ። . . . | ፲፩፻፲፫ |
| 507 | የግብጽ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልእክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ አስማን ፡ ቶፊክ ፡ ጥቅምት ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፩፻፲፰ |
| 508 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. የጦር ፡ ሠራዊትንና ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ የመለማመጃ ፡ ስልት ፡ በጐበኙበት ፡ ጊዜ ፡ ለዝቅተኛ ፡ ሹማምንቶችና ፡ ለተራ ፡ ወታደሮች ፡ ያስነገሩት ፡ የንጉሣዊ ፡ ቸሮታ ፡ ትእዛዝና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረ ፡ ቃል ። . . . . . . . . . . . . . . | ፲፩፻፳ |



| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 509 | የቤጌምድርና ፡ የሰሜን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ በዓለ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ለማበርከት ፡ አስቦ ፡ ልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ በጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ በክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አሥራተ ፡ ካሣ ፡ አማካይነት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ነገሥትና ፡ ለግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ ሲያቀርብ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢውና ፡ የድርጅቱ ፡ ኮሚቴ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተከበሩ ፡ ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ ረታ ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . | ፲፩፻፳፪ |
| 510 | የኢጣልያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ክቡር ፡ ሙሴ ፡ አልቤርቶ ፡ ቤርዮ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ ላደረጉት ፡ ንግግር ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፩፻፳፮ |
| 511 | የጃፓን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ቪጃሩ ፡ ዮሳኖ ፡ ጥቅምት ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፩፻፳፯ |
| 512 | የኤርትራ ፡ ሕዝብ ፡ ፳፫ኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ምክንያት ፡ በማድረግ ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለማበርከት ፡ ያዘጋጀውን ፡ መታሰቢያ ፡ የኤርትራ ፡ ችፍ ፡ ኤግዚኩቲፍ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ አስፍሐ ወልደሚካኤል ፡ ጥቅምት ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . | ፲፩፻፳፱ |

ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

513 የትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘ
ውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ያዘጋጀውን ፡
የወርቅ ፡ ሐውልትና ፡ የወርቅ ፡ ጋሻ ፡ ጥቅምት ፡ ፳፪ ፡
ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በጠቅላይ ፡ ገዢው ፡ በልዑል ፡
ራስ ፡ ሥዩም ፡ መንገሻ ፡ አማካይነት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ
ነገሥት ፡ ሲያበረክቱ ፡ ክቡር ፡ የአክሱም ፡ ንቡረ ፡ እድ፡
ገብረ ፡ መስቀል ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታ
ቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፬፻፴፪

514 የበጐ ፡ አድራጐት ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት፡
የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ያዘጋጁትን ፡ መታሰቢያ ፡
ጥቅምት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ለግርማዊ ፡ ንጉ
ሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ አቶ ፡ መኰንን ፡ ዘውዴ ፡ በማ
ኅበሩ ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነ
ታቸው ፡ የተነገረ ፡ አጭር ፡ መሪ ፡ ቃል ። . . . . . . . . . ፲፬፻፴፱

515 ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ስለ ፡ ፳፭ኛው ፡ ዓ
መት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በመናገሻ ፡ ቅዱስ ፡
ጊዮርጊስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቅጽር ፡ ውስጥ ፡ በተደረ
ገው ፡ የሬፍሬሽመንት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡
ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ የተከበሩ ፡ ደጃዝማች ፡ መን
ገሻ ፡ ውቤ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ
ሥት ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፬፻፵

516 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
፳፭ኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ በተ
ከበረበት ፡ በጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በፓ
ርላሜንት ፡ የተናገሩት ፡ የዙፋን ፡ ቃል ። . . . . . . . . . . ፲፬፻፵፪



ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

517 የሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ እንደ
ራሴ ፡ በክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ አማካይነት
የወከላቸው ፡ የያውራጃው ፡ አገር ፡ ገዢዎችና ፡ ታላላቅ፡
የመንግሥት ፡ ሠራተኞች ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡
፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡
ፊት ፡ ቀርበው ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡
ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በጥበባዊ ፡
ቅርጽ ፡ የተዘጋጀውና ፡ የኢትዮጵያ ፡ ካርታ ፡ ያለበትን ፡
ስጦታ ፡ ባቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ክቡር ፡ ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተ
ሰማ ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መ
ልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፬፻፶፯

518 የወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘ
ውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ያዘጋጀውን ፡
የግሩማን ፡ አናብስት ፡ ሥዕል ፡ ጥቅምት ፡ ፳፮ ፡ ቀን ፡
፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በልዑል ፡ አልጋወራሽ ፡ አስፋወሰን ፡
አማካይነት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥትና ፡ ለግርማ
ዊት ፡ እቴጌ ፡ ሲያበረክት ፡ የወሎ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡
ዲሬክተር ፡ አቶ ፡ በላይ ፡ መርሻ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡
ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . ፲፬፻፶፱

519 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡
፳፭ኛውን ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ለማክበር ፡
የመጡትን ፡ የዓለም ፡ ጋዜጠኞች ፡ ጥቅምት ፡ ፳፯ ፡ ቀን፡
፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡
ተቀብለው ፡ ሲያነጋግሯቸው ፡ ሳሉ ፡ የፈረንሳይ ፡ ራዲዮ
ዲፉዚዮን ፡ ባልደረባ ፡ ሙሴ ፡ ቫር ፡ አይዝሐቅ ፡ ምስጋና
ቸውን ፡ በንግግር ፡ ከገለጹ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡
የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፬፻፷፮

| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 520 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ስለ ፡ ፳፫ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ክብር ፡ የተዘጋጀውን ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ኤግዝቢሽን ፡ ጥቅ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የን ግድና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ጌታሁን ፡ ተሰማ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊ ነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። | ፲፬፻፷፱ |
| 521 | በአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ የሚገኙ ፡ የሕንድ ፡ ተወላጆች ፡ በማኅታማ ፡ ጋንዲ ፡ ስም ፡ ያቋቋሙትን ፡ የማዋለጃ ፡ ሆስፒታል ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የኰሙኒ ቴው ፡ ፕሬዚዳንትና ፡ የሕንድ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት አምባሳደር ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ መልስ ። | ፲፬፻፸፪ |
| 522 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አድዋ ፡ አደባባይ ፡ ላይ ፡ ከጥሩ ፡ ድንጋይ ፡ የተሠራውን የአንበሳ ፡ ሐውልት ፡ ጥቅምት ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. መርቀው ፡ ሐውልቱን ፡ ሲገልጹ ፡ የከተማው ፡ ገዥ ፡ ክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይነህ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ። | ፲፬፻፹ |
| 523 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ገፈርሳ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የሠራ ውን ፡ የውሀ ፡ ግድብ ፡ ኅዳር ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ ክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ ፡ በላይ ነህ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። | ፲፬፻፹፬ |



| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 524 | የእስፓኝ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ፡ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ገርዜ ፡ ቤልካስታኖ ፡ ኅዳር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታ ቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። | ፲፬፻፹፰ |
| 525 | የአዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ፳፫ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ክብር ፡ ኅዳር ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ማታ ፡ በግዮን ፡ ሆቴል ፡ ባደረገው ፡ የራት ፡ ግ ብዣ ፡ ላይ ፡ የከተማው ፡ ገዥ ፡ ክቡር ፡ ከንቲባ ፡ ዘውዴ በላይነህ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተ ሰጠ ፡ መልስ ። | ፲፬፻፹፱ |
| 526 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፳፫ኛውን ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ ምክ ንያት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ማደሪያ ፡ መሬትና ፡ ስለ ፡ ባንክ ፡ መቋቋም ፡ ስለወንጀለኛ ፡ ምሕረትና ፡ ቅጣትን ፡ ስለመቀነስ ፡ ኅዳር ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. ያስነገ ሩት ፡ ያዋጅ ፡ ቃልና ፡ ስለ ፡ መሠረተ ፡ ትምህርት ፡ የ ወጣ ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ። | ፲፬፻፺፩ |
| 527 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ለ፳፫ኛው ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ የተዘጋጀውን ኢንተርናሽናል ፡ ኤግዚቢሽን ፡ ኅዳር ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሲጐበኙ ፡ የጉራጌ ፡ ሕዝብ ፡ በአንድ ፡ ድርጅት ፡ አማካይነት ፡ እንደአገሩ ፡ ባህል ፡ ያዘጋጃቸውን ፡ ቤቶችና ፡ ዕቃዎች ፡ ከተመለከቱ ፡ በኋላ የድርጅቱ ፡ ፕሬዚዳንት ፡ አቶ ፡ አልፍሬድ ፡ ሻፊ ፡ የተና ገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። | ፲፬፻፺፫ |

| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| 528 | የሐረር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሕዝብ ፡ ለ፳፭ኛው ፡ ዓመት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ኢዮቤልዩ ፡ መታሰቢያ ፡ ያዘጋጀውን ፡ ገጸ ፡ በረከት ፡ ኅዳር ፡ ፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ እንደራሴ ፡ በክቡር ፡ ኰሎኔል ፡ ከፍሌ ፡ ዕርገቱ ፡ አማካይነት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ እንደራሴው ፡ ክቡር ፡ ኰሎኔል ፡ ከፍሌ ፡ ዕርገቱና ፡ አቶ ፡ አክሊለ ፡ ደጀን ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . | ፲፬፻፹፰ |
| 529 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ኅዳር ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ደራስያንን ፡ በቤተ ፡ መንግሥታቸው ፡ ተቀብለው ፡ ለያንዳንዳቸው ፡ የደራሲነት ፡ ምልክት ፡ መታሰቢያ ፡ በሸለሟቸው ፡ ጊዜ ፡ የተከበሩ ፡ ደጃዝማች ፡ ደምሴ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤልና ፡ አቶ ፡ ያሬድ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ንግግር ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ። . . . . . . . . | ፲፬፻፺፰ |
| 530 | ትምህርቱን ፡ ፈጽሞ ፡ ከአሜሪካን ፡ የተመለሰ ፡ ዘውዴ ፡ ገብረ ፡ መድህን ፡ የተባለ ፡ ወጣት ፡ ኅዳር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፭፻ |
| 531 | የዩጎስላቢያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክቡር ፡ ማርሻል ፡ ጆሴፍ ፡ ብሮዝ ፡ ቲቶ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመጐብኘት ፡ መጥተው ፡ ታኅሣሥ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ዓ. ም. ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲቀበሉዋቸው ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . - | ፲፭፻፫ |



| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| 532 | ታኅሣሥ ፡ ፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. ከማታው ፡ በ፪ ፡ ሰዓት በዩጐስላቢያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ለክቡር ፡ ማርሻል ፡ ቲቶ ፡ ክብር ፡ በገነተ ፡ ልዑል ፡ ቤተ መንግሥት ፡ በተደረገው ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ክቡር ፡ ማርሻል ፡ ቲቶ ፡ የሰጡት ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፭፻፭ |
| 533 | ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ምጽዋ ፡ ላይ ፡ አዲስ ፡ የተቋቋመውን ፡ የመርከበኞነት ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በኤርትራ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ እንደራሴ ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሳይ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . | ፲፭፻፲ |
| 534 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በአሥመራ ፡ ከተማ ፡ አዲስ ፡ የተሠራውን ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ፪ኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. መርቀው ፡ ሲከፍቱ የትምህርት ፡ ቤቱ ፡ ዲሬክተርና ፡ በኤርትራ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ እንደራሴ ፡ ክቡር ፡ ቢትወደድ ፡ አንዳርጋቸው ፡ መሳይ ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፭፻፲፰ |
| 535 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፶፰ ፡ ዓ. ም. በካምቦኒ ፡ ኮሌጅ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትያትር ፡ ለማየት ፡ በተገኙ ፡ ጊዜ ፡ አባ ፡ ጋስፓሪ ፡ ያደረጉት ፡ ንግግርና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . | ፲፭፻፳፩ |

| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 536 | የኢትዮጵያ ፡ ዜግነት ፡ ያላቸው ፡ ክልሶች ፡ በእብነ ፡ በረድ ፡ የተሠራና ፡ ታሪካዊ ፡ ጽሑፍ ፡ ያለበትን ፡ አንድ ፡ መታሰቢያ ፡ ጥር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አቅርበው ፡ ባበረከቱ ፡ ጊዜ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረ ፡ ቃል ። ................ | ፲፰፻፳፰ |
| 537 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ አጼ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጥር ፡ ፳ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. በአሥመራ ፡ የተግባረ፡ ዕድን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲጐበኙ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል። | ፲፰፻፳፯ |
| 538 | ለእርሻ ፡ ትምህርት ፡ ወደጀርመን ፡ አገር ፡ የሚሔዱ ፡ ፲፰ ፡ ወጣቶች ፡ ጥር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተነገረ ፡ ምክር ። ............... | ፲፰፻፳፯ |
| 539 | ለትምህርት ፡ ወደ ፡ አሜሪካ ፡ የሚሔዱ ፡ ፱ ፡ ወጣቶች ፡ የካቲት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከወጣቶቹ ፡ አንዱ በጓደኞቹ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ። .......... | ፲፰፻፳፰ |
| 540 | የመስኰብ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ክቡር ፡ ቦሪስ ፡ ኢባኖቪች ፡ የካቲት ፡ ፺ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተናገሩትና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። ........................ | ፲፰፻፴ |



| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 541 | ለሕንፃ ፡ ሥራ ፡ ወደ ፡ ስዊድን ፡ አገር ፡ የሚሄዱ ፡ ፪ ፡ ወጣቶች ፡ የካቲት ፡ ፲፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከወጣቶቹ ፡ አንዱ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ። .................. | ፲፰፻፴፩ |
| 542 | የ፲፪ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጆች ፡ ዘጠነኛውን ፡ ዓመታዊ ፡ ጉባኤ ፡ አድርገው ፡ ከፈጸሙ ፡ በኋላ ፡ የካቲት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ የትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ አቶ ፡ ውሂብ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በሌሎች ፡ ሁሉ ፡ ስም ፡ ሆነው ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ። .............. | ፲፰፻፴፫ |
| 543 | የከብት ፡ ሕክምና ፡ ለመማር ፡ ወደ ፡ አውስትራሊያ ፡ ሲድኒ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ የሚሔዱ ፡ ሁለት ፡ ወጣቶች ፡ የካቲት ፡ ፳፯ ፡ ቀን፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲሰናበቱ ፡ ከወጣቶቹ ፡ አንዱ ፡ የተናገረው ፡ ቃልና ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መሪ ፡ ቃል ። ........................... | ፲፰፻፴፱ |
| 544 | በሎንዶን ፡ ፲፫ ፡ ዓመት ፡ ያህል ፡ የሕክምና ፡ ትምህርት ፡ ሲማር ፡ ቆይቶ ፡ የመጣው ፡ አሥራት ፡ ወልደየስ ፡ የሚባለው ፡ ወጣት ፡ የካቲት ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ እጅ ፡ ከነሳ ፡ በኋላ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ለወጣቱ ፡ የሰጡት ፡ መሪ ፡ ትእዛዝ ። ....................... | ፲፰፻፷፩ |

ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

566 የሶቪዬት ፡ ዩኒየን ፡ ሶሲያሊስት ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ መስከረም ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳ ቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . ፲፮፻፰

567 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መስከረም ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ለጐልድ ፡ ኮስት ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ለክ ዋሜ ፡ ንክሩማህ ፡ ያስተላለፉት ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ቴሌግራም ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፮፻፲

568 በበጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሲማሩ ፡ የነበሩት ፡ ፲፫ ፡ ወን ዶችና ፡ ሴቶች ፡ ተማሪዎች ፡ ለትምህርት ፡ ወደ ፡ እሥ ራኤል ፡ እንዲሄዱ ፡ ስለተፈቀደላቸው ፡ መስከረም ፡ ፲፫ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀር በው ፡ ሲሰናበቱ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . . . ፲፮፻፲፩

569 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መስከረም ፡ ፳፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ዓ. ም. በአየር ፡ ኃይል ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ትምህርታ ቸውን ፡ ለፈጸሙ ፡ ካዴቶች ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ሲሰጡ ፡ የተናገሩት ፡ መሪ ፡ ቃል ። . . . . . . . . . . . . ፲፮፻፲፪

570 የምዕራባዊ ፡ ጀርመን ፡ ፌዴሬሺን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ መስከረም ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብ ዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፮፻፲፫

571 የሱዳን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለ ሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ጥቅምት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ለግርማዊ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . ፲፮፻፲፯



ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

572 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሕንድን ፡ ለመጐብኘት ፡ ስለሚ ሔዱ ፡ ጥቅምት ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚኖሩ ፡ ሕንዳውያን ፡ የመሰናበቻ ፡ በዓል ፡ አድርገው ፡ ያሳዩትን ፡ የጨዋታ ፡ ትርዕይት ፡ ከተመለ ከቱላቸው ፡ በኋላ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . . . ፲፮፻፲፱

573 የዩጐስላቭ ፡ ሬፑብሊክ ፡ ፌዴራል ፡ ፖፒለር ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ጥቅምት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤ ያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . ፲፮፻፳፩

574 የእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ጥቅምት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደ ረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፮፻፳፫

575 የስዊስ ፡ ኰንፌደራሲዮን ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ጥቅ ምት ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያ ቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። . . . . . . . . ፲፮፻፳፮

576 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ቦምቤይ ፡ ከተማ ፡ ሲገቡ ፡ የከተማው ፡ ከንቲባ ፡ በክብር ፡ ተቀብለው ፡ ላደረገላቸው ፡ የደስታ ፡ መግለጫ ፡ ንግግር ፡ የሰጡት ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . ፲፮፻፳፯

577 ጥቅምት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የኬራላ ፡ አገረ ፡ ገዥ ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ክብር ፡ ባደረጉት ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . ፲፮፻፳፱

578 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ሕንድን ፡ በመጐብኘት ፡ ላይ ፡ ስለሆኑ ፡ ለኢት ዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ያስተላለፉትና ፡ በፓርላሜት ፡ የተነ ገረ ፡ የግርማዊነታቸው ፡ መልእክት ። . . . . . . . . . . ፲፮፻፴

ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

579 የባንጋሎ ፡ ዋና ፡ ሚኒስትር ፡ ጥቅምት ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ስለ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የዘውድ ፡ በዓል ፡ ክብር ፡ ባደረጉት ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ንግግር ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። ........ ፲፪፻፴፪

580 ኅዳር ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የጃፓንን ፡ አገር ፡ ሲጐበኙ ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ስለግርማዊነታቸው ፡ ክብር ፡ የተናገሩት ፡ ቃልና፡ ከግርማዊነታቸው ፡ የተሰጠ ፡ መልስ ። ........... ፲፪፻፴፫

581 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኅዳር ፡ ፲፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም ከጃፓን ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ቶኪዮ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ለጃፓን ፡ ሕዝብ ፡ ያደረጉት ፡ ንግግር ። ........... ፲፪፻፴፭

582 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኅዳር ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከቶኪዮ ፡ ለመነሣት ፡ በአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ ተገኝተው ፡ ሳሉ ፡ ከመነሣታቸው ፡ በፊት ፡ ለጋዜጠኞች፡ ያስታወቁት ፡ ቃል ። .................. ፲፪፻፴፮

583 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ኅዳር ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. አዲስ ፡ አበባ ፡ ሲገቡ ፡ በአውሮፕላን ፡ ማረፊያ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። ................. ፲፪፻፴፯

584 የቤኔዙዌላ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የተላኩትን ፡ ከፍተኛ ፡ የክብር ፡ ኒሻን ፡ ታኅሣሥ ፡ ፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የቤኔዙዌላ ፡ አምባሳደር ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። .................. ፲፪፻፵፩

585 የቼኰዝሎቫኪያ ፡ ሬፑብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ታኅሣሥ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። ............. ፲፪፻፵፪



ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ

586 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከጦር ፡ ሠራዊት ፡ ውጭ ፡ ለሆኑ ወታደሮችና ፡ መኰንኖች ፡ መተዳደሪያ ፡ እንዲሆን ፡ ያቋቋሙትን ፡ አቦምሳ ፡ የተባለውን ፡ ስፍራ ፡ ታኅሣሥ ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ሲጐበኙ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። ......................... ፲፪፻፵፬

587 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በምጽዋ ፡ ከተማ ፡ አዲስ ፡ የተቋቋመውን ፡ ዝቅተኛ ፡ የመርከብ ፡ መኰንኖች ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ጥር ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. መርቀው ሲከፍቱ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። ............. ፲፪፻፶

588 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የኢትዮጵያና ፡ የስዊድን ፡ የመሐንዲስ ፡ ሕንፃ ፡ ኰሌጅን ፡ የካቲት ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. መርቀው ፡ ሲከፍቱ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። ... ፲፪፻፶፫

589 የዴንማርክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ የካቲት ፡ ፮ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። ....................... ፲፪፻፶፯

590 በግሪክ ፡ አገርና ፡ በጀርመን ፡ አገር ፡ ከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ሲማሩ ፡ ቆይተው ፡ የተመለሱ ፡ ተማሪዎች ፡ የካቲት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ እጅ ፡ ሲነሱ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። ...... ፲፪፻፷

591 ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ የካቲት ፡ ፲፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተገኝተው ፡ ሲጐበኙ ፡ ለተማሪዎቹ ፡ የተናገሩት ፡ የምክር ፡ ቃል ። ......................... ፲፪፻፷፭

592 የዩናይትድ ፡ እስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ ምክትል ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ክቡር ፡ ሚስተር ፡ ኒክሰን ፡ መጋቢት ፡ ፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. አዲስ ፡ አበባ ፡ ሲገቡ ፡ ለሕዝቡ ፡ የተናገሩት ፡ ቃል ። ......................... ፲፪፻፷፯

| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 606 | የኢትዮጵያና ፡ የኤርትራ ፡ አንድነት ፡ ማኅበር ፡ አባሎች ፡ ግንቦት ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ለልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ ሐውልት ፡ ስለማቆም ፡ ጉዳይ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፮፻፺፰ |
| 607 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ግንቦት ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ለሕዝባቸው ፡ የሰጡት ፡ ጠቃሚ ፡ ምክር ። | ፲፮፻፺፱ |
| 608 | በልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ ሞት ፡ ምክንያት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ መሪዎችና ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ ክፍሎች ፡ በየጊዜው ፡ ለግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት የተላኩ ፡ የኀዘን ፡ መግለጫ ፡ ቴሌግራሞች ። | ፲፯፻ |
| 609 | የፖላንድ ፡ ሬፐብሊክ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ግንቦት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ የተነገሩ ፡ ቃሎች ። | ፲፯፻፲፩ |
| 610 | የባቲካን ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ ሚኒስትር ፡ ግንቦት ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተነገሩ ፡ ቃሎች ። | ፲፯፻፲፯ |
| 611 | የየረርና ፡ የከረዩ ፡ አውራጃ ፡ ሕዝቦች ፡ ለልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ አንድ ፡ ቀዋሚ ፡ መታሰቢያ ፡ ለማቆም ፡ ስላሰቡ ፡ ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ሲያመለክቱ ፡ የተነገሩ ፡ ቃሎች ። | ፲፯፻፲፱ |
| 612 | በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ ጥንታውያን ፡ እስካዎቶች ፡ ስለ ፡ ልዑል ፡ መኰንን ፡ ሞት ፡ የተሰማቸውን ፡ ጥልቅ ፡ ኀዘን ፡ ለግርማዊነታቸው ፡ ሲገልጡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፯፻፳፪ |



| ተራ ፡ ቍጥር ፡ | አርእስተ ፡ ነገር ። | ገጽ |
|---|---|---|
| 613 | የሕንድ ፡ አምባሳደርና ፡ በአዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኙ ፡ የሕንድ ተወላጆች ፡ ሰኔ ፡ ፲፫ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ለልዑል ፡ መኰንን ፡ መስፍነ ፡ ሐረር ፡ መታሰቢያ ፡ የሚሆን ፡ ኻያ ፡ ሺህ ፡ ብር ፡ ሲያበረክቱ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፯፻፳፰ |
| 614 | የዩናይትድ ፡ ስቴትስ ፡ ኦፍ ፡ አሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ አምባሳደር ፡ ሰኔ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. የሹመት ፡ ደብዳቤያቸውውን ፡ ሲያቀርቡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፯፻፴ |
| 615 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሰኔ ፡ ፲፰ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም በፖሊስ ፡ ፈጥኖ ፡ ደራሽ ፡ ሻለቃ ፡ ሰፈር ፡ የራዲዮ ፡ ክፍል ፡ ሠራተኞችንና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቴክኒክ ፡ ትምህርት ፡ ተማሪዎችን ፡ ሲጐበኙ ፡ የሰጡት ፡ መሪ ፡ ቃል ። | ፲፯፻፴፫ |
| 616 | በአዲስ ፡ አበባ ፡ ዩኒቬርሲቲ ፡ ኰሌጅ ፡ የተመደበላቸውን ፡ ትምህርት ፡ ጨርሰው ፡ ፈተናውን ፡ ያለፉ ፡ ፵፭ ፡ ወጣቶች ፡ የምስክር ፡ ወረቀታቸውን ፡ ሐምሌ ፡ ፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊነታቸው ፡ ሲቀበሉ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፯፻፴፯ |
| 617 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አንደኛውን ፡ ዓመት ፡ የደን ፡ በዓል ፡ ስማክበር ፡ ሐምሌ ፡ ፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ. ም. በገነት ፡ ከተማ ፡ ተገኝተው ፡ በዓሉን ፡ ሲያከብሩ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፯፻፵፯ |
| 618 | የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አማካሪዎች ፡ ሐምሌ ፡ ፲፪ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. ከግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ፊት ፡ ቀርበው ፡ ለዕረፍት ፡ ሲሰናበቱ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፯፻፵፱ |
| 619 | ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሐምሌ ፡ ፲፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፱ ፡ ዓ. ም. በትምህርታቸው ፡ ብልጫ ፡ ላገኙ ፡ ተማሪዎች ፡ ሽልማት ፡ ሲሰጡ ፡ የተደረጉ ፡ ንግግሮች ። | ፲፯፻፶፪ |

